Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ስለ ስፒከቫክስ/Spikevax (ሞደርና/Moderna) ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መረጃ

መጨረሻ ወቅታዊ የሆነው: ቀን 15 መስከረም/September 2021

## ስለ ክትባቱ

**ሞደርና (Moderna)** ክትባት ሲሆን ይህም ሰዎችን በኮቪድ/COVID-19 ከመታመም መከላከል የሚችል ክትባት ነው። ሁለት ጊዜ መጠን/doses ክትባት መውሰድ እንደሚያስፈልግ፤ ይህም በአብዛኛው ከ4 እስከ 6 ሳምንታት አፈላላይነት (ለየት ባሉ ሁኔታዎች ላይ ረጅም ባሉ ልዩነት) የሚሰጥ ይሆናል። የሞደርና ኮቪድ/Moderna COVID-19 ክትባት ምንም ዓይነት ህይወት ያለው ቫይረስ እንደማይዝና ለኮቪድ/COVID-19 አጋልጦ ሊሰጥዎ አይችልም። ስፒክ ፕሮቲን/spike protein ለተባለ የSARS-CoV-2 ቫይረስ ጠቃሚ የሆነ በራሄ ጂናዊ ዝርያ መለያ/genetic code እንደያዘ ነው። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ፤ ሰውነትዎ ለስፒክ ፕሮቲን/spike protein እንዲባዛ ያደርጋል። ከዚያም ለኮቪድ/ COVID-19 ምክንያት የሆነውን SARS-CoV-2 ቫይረስን ለይቶ ለመዋጋት የርስዎ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ይማራል። በራሄ ጂናዊ ዝርያ መለያ/genetic code በፍጥነት በሰውነት ይቋረጣል።

ኮቪድን/COVID-19 ለመከላከል የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ለማግኘት የሚፈቀድለት በመረጃ ወረቀቱ ካሉት ጥቂት ምክንያቶች ባሻገር እያንዳንዱ ሰው መውሰድ አለበት። ክትባት መውሰድ በፈቃደኛነት ነው። ስለ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ በተመለከተ የሚያሳስብ ወይም ጥያቄዎች ካለዎት፤ ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ከርስዎ ክትባት አቅራቢ እና/ወይም ከአጠቃላይ ሀኪምዎ/GP ጋር መነጋገር ነው።

## የክትባቱ ጥቅሞች

በጣም ታላቅ በሆኑ ክሊኒካል ሙከራዎች እንዳሳዩት፤ ሞደርና/Moderna ክትባት እድሚያቸው ≥12 ዓመት ለሆኑ እና ከዚያ በላይ ለሆኑት ሰዎች በጥሩ ሁኔታ ኮቪድ/COVID-19 እንደሚከላከል ነው። ሁለት መጠን/doses የሞደርና/Moderna ክትባት ከወሰዱት ሰዎች በኮቪድ/ COVID-19 የሚታመሙት ክትባት ካላገኙት ጋር ሲነጻጸር ከመቶ ወደ 94 እጅ ዝቅ እንዳለ ነው። እንዲሁም እድሚያቸው ከ65 ዓመት በላይ ለሆኑት ሰዎች (86%) እና እድሚያቸው በ 12-17 ዓመት መካከል ላሉ ታዳጊ ወጣቶች ክትባቱ ጥሩ ውጤት እንዳስገኘ ነው።

ሁለተኛ መጠን/dose ኮቪድ/COVID-19 ክትባት የሚጀምረው የመጀመሪያ መጠን/dose ክትባቱን ከወሰዱ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ነው። የመጀመሪያ መጠን/dose ክትባት ጥቂት መከላከያ ቢሰጥም፤ ይህ የሚያበቃው ለአጭር ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል። የሁለተኛ መጠን/dose ክትባቱ ስኬታማ የሆነ መከላከያ ይሰጣል። ከመቶ 100 እጇ ውጤታማ የሚሆን ክትባት ስለሌለ፤ ስለዚህ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ አሁንም በኮቪድ/ COVID-19 መበከልና መታመም ሊያጋጥምዎት ይችላል። በሞደርና/Moderna ክትባት መከላከያ ለምን ያህል እንደሚቆይ አናውቅም። ስለዚህ ጉዳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንማራለን። በአሁን ጊዜ የኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለቫይረስ ስርጭት መከላከል ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ በትክክል አናውቅም። ይህ ማለት ሰዎች ክትባት ቢወስዱም በኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ እንደሚበከሉ እና ምንም እንኳን የበሽታ ምልክቶች ባይኖርባቸውም ወይም አነስተኛ ምልክቶች ቢታይባቸውም ነገር ግን ቫይረሱን ለሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

ለዚህ ነው ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ መከላከያ እርምጃዎችን መቀጠል ያስፈለገ:

- የአካል እርቀት
- እጅን መታጠብ
- የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ማጥለቅ
- የኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ እና እንደ የርስዎ አስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ አስፈላጊነት በመገለውያ ቦታ መቆያ ነው።

ሁለቱን መጠን/ doses የሞደርና/Moderna ክትባት ቢወስዱም፤ በአካባቢዎ ባለ የጤና ጥበቃ ባለስልጣን ለምርመራ ቅድመ ሁኔታ መሰረት የሚያሟላ የበሽታ ምልክቶች (ለምሳሌ፡ ትኩሳት፤ ሳል፤ የጉሮሮ ህመም) ካሉ አሁንም ኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማድረግ።

## ይህን ክትባት ማን ማግኘት እንደሚችል

እድሚያቸው ≥12 ዓመት ለሆኑ ሰዎች የስፒከያክስ/Spikevax (ሞደርና/Moderna) ክትባትን እንዲጠቀሙ በህክምና ጥራት አስተዳደር (TGA) ጊዜያዊ ፈቃድ እንደሰጠ ነው።

## ማን ነው ይህን ክትባት ማግኘት የማይችለው

የሚከተሉት ከነበረብዎት ይህን ክትባት መውሰድ የለብዎትም:

- ቀደም ብሎ በተሰጠ መጠን/dose የ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም Moderna ወይም Comirnaty (Pfizer)) ላይ አለመስማማት/anaphylaxis (ይህ ከፍተኛ የአለርጂክ ዓይነት) ተፈጥሮ ከነበረ
- በሆነ ቫይረስ ይዘት፤ ለ polyethylene glycol (PEG) ያካተተ ከተጋለጡ በኋላ አለመስማማት/anaphylaxis
- ቀደም ብሎ በተሰጠ መጠን/dose የ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም Moderna ወይም Pfizer) በችግር myocarditis እና/ወይም pericarditis ላይ አስተዋጽኦ አድርጎ ከሆነ
- ልምድ ባለው የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ወይም በልዩ ህክምና ባለሙያ ግምገማን በመከተል፤ ቀደም ብሎ በተሰጠ መጠን/dose የ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም Moderna ወይም Pfizer) ላይ ምንም ዓይነት ሌላ ከባድ ችግር ካልታወቀ ነው።

## ክትባት ለመውሰድ ጥንቃቄዎች

አንዳንድ ሁኔታዎች ላለባቸው ሰዎች ተጨማሪ ጥንቃቄ ሊያስፈልጋቸው ይችላል፤ ይህም እንደ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ለ30 ደቂቃዎች ክትትል መቆየት ወይም ለአለርጂክ ልዩ ባለሙያ ምክርን ለማግኘት። የሚከተሉት ካለብዎት ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ካለዎት መናገር:

- **ቀደም ሲል በተሰጠ መጠን/dose** ወይም በ mRNA COVID-19 ክትባት (ይህም Moderna ወይም Pfizer) ይዘት ላይ **የአለርጂ ችግር ተፈጥሮ** ከነበር
- **በሌላ ክትባቶች ወይም መድሃኒቶች ላይ አለመስማማት/anaphylaxis መፈጠር።** ከሚወስዱት ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ጋር ትክክለኛ ያልሆኑ ንጥረ ነገሮች እንደሌለው ለማረጋገጥ፤ በርስዎ ክትባት አቅራቢ በኩል መጣራት ይችላል
- በአሁኑ ጊዜ ከmastocytosis ችግር ጋር የታወቀ ህክምና የሚያስፈልገው አለመስማማት/anaphylaxis ካለ ነው

**የመድማት ችግር ካለብዎት** ወይም **የደም ማቅጠኛ መድሃኒት** (anticoagulant) የሚወስዱ ከሆነ፤ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ መናገር። በጅማት ውስጥ መርፌ መወጋት ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ለመወሰን የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ ሊረዳዎ እንደሚችልና መርፌውን ለመወጋት ጥሩ ጊዜ መቸ እንደሆነ ለመወሰን ይረዳዎታል።

## ክትባቱን ከመውሰድ በፊት ለየት ባሉ ሁኔታዎች ለመነጋገር

### ሰዎች ለሞደርና/Moderna ሲወስዱ የቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታዎች

ከዚህ የሚከተሉት ማንኛውም ሁኔታ ጋር ታሪክ ላለባቸው ሰዎች ሞደርና/Moderna ክትባት ማግኘት ሲችሉ ነገር ግን ክትባቱን ለመውሰድ ስለ በጣም ጥሩ ጊዜ እና ስለሚቀርብ ተጨማሪ ጥንቃቄ ከአጠቃላይ ሀኪም/GP፤ ከበሽታ መከላከያ ክትባት ልዩ ባለሙያ ወይም ከልብ ባለሙያ/cardiologist ምክር ማግኘት ያስፈልጋል:

- በቅርቡ (ይህም ባለፉት 6 ወራት ውስጥ) ወይም አሁን ለልብ ህመም የሚያባብስ፤ ለምሳሌ፡ myocarditis, pericarditis, endocarditis
- የማይድን የቁርጥማት ህመም (ይህም ተግባራዊ ከሆነ የልብ ህመም/myocardial እብጠት) ወይም የማይድን ሀይለኛ የልብ በሽታ
- የማይድን ከፍተኛ የልብ መቆም መባባስ

## የተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ አሰራር ሀይል ላለባቸው ሰዎች (immunocompromise)

በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ጋር ባሉት ሰዎች የሚካተት ለበሽታ መቋቋሚያ አሰራር ሀይል የሚያዳክም የጤና ህክምና ሁኔታ ላለባቸው ሰዎች ነው። እንዲሁም ለበሽታ መቋቋሚያ አሰራር ሀይል የሚያዳክም መድሃኒቶችን ለሚወስዱ ሰዎች ያካትታል።

በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ አሰራር ሀይል ጋር ላሉት ሰዎች የኮቪድ/COVID-19 ክትባትን እንዲወስዱ የአውስትራሊያ መንግሥት ብጥብቅ ያሳስባል። ሞደርና/Moderna ህይወት ያለው ክትባት አይደለም። በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ላሉ ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ነው።

በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ካሉት ሰዎች የሚካተት ከሄችአይቪ/ HIV ጋር ለሚኖሩና በኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ ሞትን ያካተተ በከፍተኛ ህመም ችግር ላይ ለሚጋለጡ ሰዎች ይሆናል።

በሞደርና/Moderna ክሊኒካል ሙከራዎች ከጥቂት የተረጋጋ ሄችአይቪ/ HIV ካለባቸው ቡድኖች ባሻገር በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ያሉትን ሰዎች አላካተተም። በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ አሰራር ሀይል ላሉት ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸር የሞደርና/Moderna ክትባት ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ አናውቅም። ሞደርና/Moderna ክትባት ለአጠቃላይ ህዝብ እንደመሆኑ መጠን በተዳከመ በሽታ መቋቋሚያ ሀይል ላሉት ሰዎች ውጤታማ ላይሆን ይችል ይሆናል። ሌሎች የመከላከያ እርምጃዎችን፣ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ እንደ የአካል እርቀትን መቀጠሉ ጠቃሚ ነው።

## እርጉዝ ወይም ጡት ስለሚያጠቡ ሴቶች

ለእርጉዝ ሴቶችና ታዳጊ ወጣቶች መደበኛ ከሆኑ የ mRNA-based COVID-19 ክትባቶች አንዱን መቅረብ አለበት። በማንኛውም የእርግዝና ደረጃ ፕፊዘር/Pfizer ወይም ሞደርና/Moderna ክትባትን መውሰድ። ለማርገዝ የሚሞክሩ ከሆነ ለክትባት መውሰድ ጊዜ ማራዘይ እንደሌለብዎ ወይምክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ላለማርገዝ የሚለውን ማስወገድ።

ከኮቪድ/COVID-19 ጋር ያሉት እርጉዝ ሴቶች በከፍተኛ ህመም የመጋለጥ ችግር እንደሚጨምርና ለእርግዝና ተቃራኒ የሆነ ውጤት ያስከትላል። የትክክለኛ ዓለም ማስረጃ እንደሚያሳየው ለእርጉዝና ለሚያጠቡ ሴቶች የሞደርና/Moderna ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ነው። ክትባቱን መቸ እንደሚወሰድ በተመለከተ ከርስዎ ጤና ባለሙያ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

የእናት ጡት የሚያጠቡ ከሆነ፣ የሞደርና/Moderna ክትባት መውሰድ ይችላሉ። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ጡት ማጥባቱም ማቆም አያስፈልግም።

## ከኮቪድ/COVID-19 ታሪክ ጋር ላሉ ሰዎች

ቀደም ሲል ኮቪድ/COVID-19 ከነበረብዎት፣ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ መናገር። ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከመውሰድዎ በፊት ከበሽታው ከዳኑ በኋላ እስከ ስድስት ወራት መጠበቅ እንዳለብዎ። በአቅራቢዎ በኩል ምክር ሊሰጥዎ ይችላል። በኮቪድ/COVID-19 ቀጣይ የሆነ ህመም ካለብዎት፣ ክትባቱን ለመውሰድ በጣም ጥሩ ጊዜ መቸ እንደሆነ ከህክምና አቅራቢ ሀኪምዎት ጋር መነጋገር።.

## ሞደርና/Moderna እና ህጻናት

እድሚያቸው ≥12 ዓመት ወይም ከዚህ በላይ ለሆኑት ሰዎች ሞደርና/Moderna ክትባትን ለመጠቀም ጊዚያዊ ፈቃድ እንዳገኘ እና ከዚህ በታች ለሆኑት ወጣቶች መስጠት አይቻልም።

## ለሞደርና/Moderna ደህንነት ስለማረጋገጥ

ለክትባት ምርመራ ጥናት የገንዘብ እርዳታ በመጨመሩ እና ለምርመራ ጥናቶች በጣም ብዙ ቁጥሮች ያሉት ፈቃደኞች መጠቀም ስለተቻለ ለሞደርና/ Moderna እና ሌሎች ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች በፍጥነት እንዲመረት አድርጓል። ሰፋ ባለ ክሊኒካል ሙከራ ላይ ወደ 30,000 ሰዎች እንደተሳተፉና ሞደርና/Moderna ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀና ውጤታማ እንደሆነ ያሳውቃል።

አውስትራሊያ ውስጥ ላሉት ክትባቶች በሙሉ በ TGA በኩል ግምገማ ይካሄዳል። ይህም ክትባቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ የክትባቱ ደህንነት፣ ውጤታማ እና በጣም ከፍተኛ ጥራት ደረጃ እንደተመረተ ያረጋግጣል። ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ተቀባይነት አሰራር ሂደት መግለጫ በTGA ድረገጽ/TGA website ላይ ይቀርባል።

ለኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ደህንነት በሞላው የኮቪድ/COVID-19 በሽታ መከላከያ ክትባት ፕሮግራም ላይ ቁጥጥር ይደረጋል።

የቫክስዘቭሪያ/Vaxzevria (AstraZeneca) አስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባትን ከወሰዱ በኋላ ሊፈጠሩ የሚችሉ መጠነኛ ችግሮች፤ ይህም ከአነስተኛ ቁጥር የደም ፕላተለት/platelet ጋር ደም መርጋት ሪፖርቶች እንደሚደረግ ነው። የአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት የሚሰራበት ከሞደርና/Moderna የተለየ መንገድ ነው። ይህ ሁኔታ ከሞድርና/Moderna ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ስለሚገናኝ የሚያሳይ መረጃ የለም።

ሊፈጠር በሚችል ችግር ጥርጣሬ ካለ ለርስዎ ክትባት አቅራቢ ወይም ሌላ ጤና ጥበቃ ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ከዚያም እርስዎን ወክለው ለርስዎ አስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶርይ ጤና ጥበቃ መምሪያ ወይም በቀጥታ ለTGA መደበኛ ሪፖርት ይቀርባል።

በራስዎ ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ፤ ከኮቪድ/ COVID-19 ክትባቶች ጋር በተዛመደ ስለሚከሰት ችግር መረጃ ለማግኘት እባክዎ በ[TGA ድረገጽ/TGA website] ላይ ማየት።